የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

| | | |
|---|---|---|
| አሥራአምስተኛ ዓመት ቁጥር ፴<br>አዲስ አበባ መጋቢት ፳፭ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም | በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ<br>የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | 15th Year No. 30<br>ADDIS ABABA 3rd April, 2009 |


ማውጫ

CONTENTS

አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፫/፪ሺ፩ ዓ.ም

ለአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከዓለም ዓቀፍ የልማት ማህበር የተገኘው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ... ገጽ ፬ሺ፮፻፸፩

Proclamation No. 623/2009

International Development Association Financing Agreement for financing the General Education Quality Improvement Project Ratification Proclamation Page 4671

## አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፫/፪ሺ፩

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዓቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነትን ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፴፫ሚሊዮን፭፻ሺ /ሰላሳ ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ/ ኤስ.ዲ.አር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዓቀፍ የልማት ማህበር መካከል እ.ኤ.አ. ዲሴምበር ፳፱ ቀን ፪ሺ፰ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፲፭ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

በሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩ አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከዓለም ዓቀፍ የልማት ማህበር የተገኘው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፫/፪ሺ፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 623/2009

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

**WHEREAS,** A Financing Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a credit in an amount equivalent to SDR 33,500,000 (thirty three million five hundred thousand Special Drawing Rights) for financing the General Education Quality Improvement Project, was signed in Addis Ababa on the 29th day of December,2008;

**WHEREAS,** the House of peoples' Representa - tives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 24th day of March, 2009;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (2) of the Constitution it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Financing Agreement for financing the General Education Quality Improvement Project Ratification Proclamation No. 623/2009".

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፪ የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዓቀፍ የልማት ማህበር መካከል እ.ኤ.አ. ዲሴምበር ፳፱ ቀን ፪ሺ፰ በአዲስ አበባ የተፈረመው ቁጥር 4535 ET የብድር ስምምነት ፀድቋል።

## ፫. የገንዘብና ኢኮኖማ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፴፫ሚሊዮን፭፻ሺ /ሰላሳ ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ/ ኤስ. ዲ.አር በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።።

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ መጋቢት ፳፭ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 2. Ratification of the Agreement

The Financing Agreement credit number 4535 – ET, signed on December 29th, 2008 in Addis Ababa between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Finance and Economic Development

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the credit amount of SDR 33,500,000 (thirty three million five hundred thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 3rd day of April, 2009**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**